የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች የአስተዳደር ወጪ አፈጻጸም መመሪያ

(መመሪያ ቁጥር 847/2014)

የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 1113/2011 አንቀጽ 64 ንዑስ አንቀጽ (4) የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅት ከገቢ ማስገኛ ስራው ከሚያገኘው ገቢ የድርጅቱን የአስተዳደር እና የፕሮግራም ወጪዎች ለመሸፈን እንደሚያውለው የተደነገገ በመሆኑ፤

በአዋጁ አንቀጽ 63 ንዑስ አንቀጽ (3) የሃያ በመቶ ገደብ በልዩ ሁኔታ ተፈጻሚ የማይሆንባቸውን ድርጅቶች በሚመለከት ባለስልጣኑ መመሪያ እንደሚያወጣ የተደነገገ በመሆኑ፤

በአዋጁ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ (2) ከአዋጁ ዓላዎች አንዱ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች በተመዘገቡበት ዓላማ መሠረት ሥራቸውን ማከናወናቸውን በመከታተልና በመቆጣጠር የሕብረተሰቡን የላቀ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ እንደሆነ የተደነገገ በመሆኑ፤

በአዋጁ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (2) የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን ድርጅቶቹ ሥራቸውን በሕግ አግባብ ማከናወናቸውን ለማረጋገጥ አስፈላጊውን ክትትልና ቁጥጥር የማድረግ እንዲሁም በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የድርጅቶቹን ዓመታዊ የሥራና የገንዘብ እንቅስቃሴ ሪፖርት በአዋጁ መሠረት የመመርመር ሥልጣንና ተግባር የተሰጠው በመሆኑ፤

ከላይ ለተጠቀሱት የአዋጁ ድንጋጌዎች አፈጻጸም መመሪያ በማውጣት የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ሊከተሉ የሚገባቸውን አሠራር በግልጽ በመደንገግ ከባለስልጣኑ ጋር የሚኖረውን ግንኙነት ውጤታማ ማድረግ በማስፈለጉ፤

የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 1113/2011 አንቀጽ 89 ንዑስ አንቀጽ (2) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ

Civil Society Organizations' Administrative Expense Implementation Directive

(Directive No.847/2021)

Whereas; it is stipulated in Article 84 Sub-article (4) of the Civil Societies Proclamation No. 1113/2019 that a civil society organization shall use the funds obtained through income generating activities to defray its administrative and program expenses;

Whereas; Article 63 sub-article (3) of the Proclamation provides that the Authority may issue a directive regarding organizations exempted from the twenty-percent cap;

Whereas; Article 5 sub-article (2) of the of the Proclamation states that one of the Authority's objectives is to ensure utmost public benefit by supervising whether Civil Society Organizations perform their activities in accordance with their registered objectives;

Whereas; Article 6 sub-article (2), of the Proclamation granted the Authority the power to monitor and supervise that civil society organizations perform their activities in accordance with the law; and, sub-article (3) of the same article, granted the power and responsibility to examine the annual activity and financial reports of the organizations;

Cognizant of the need to issue directives for the implementation of the above-referred to provisions of the Proclamation that clearly set out procedures civil society organizations need to follow in order to ensure a fruitful working relationship with the Authority have to be put in place;

Now therefore; the Authority for Civil Society Organizations has issued this directive in accordance with the power conferred on it by virtue of Article 89 sub-article (2) of the Civil Society Organizations' Proclamation.

አውጥቷል።

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች የአስተዳደር ወጪ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 847/2014" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፣

1/ "የአስተዳደር ወጪ" ማለት ድርጅቱ ከሚያከናውነው የፕሮጀክት ሥራ ጋር ተያያዥነት የሌለው፣ነገር ግን ለድርጅቱ ሕልውና ቀጣይነት አስፈላጊ የሆነ እና ከአስተዳደር ሥራዎች ጋር የተያያዘ ወጪ ሲሆን፣ የአስተዳደር ሠራተኞች ደመወዝና ጥቅማጥቅሞችን፣ ከአስተዳደር ሥራ ጋር የተያያዘ የአላቂና ቋሚ እቃዎች ግዢን፣ የጥገናና እድሳት ወጪዎችን፣ የቢሮ ኪራይ፣ የፓርኪንግ ክፍያዎች፣ የኦዲት አገልግሎት፣ የማስታወቂያ ክፍያ፣ የባንክ አገልግሎት፣ የመብራት፣ የስልክ፣ የፋክስ፣ የውሃ፣ ኢንተርኔት፣ የፖስታና የሕትመት አገልግሎት ወጪዎችን፣ ታክስ፣ ለአስተዳደር ሥራ የሚውሉ ተሽከርካሪዎች ግዥ፣ ጥገና፣

Part One

General

1. Short Title

This Directive may be cited as the "Civil Society Organization's Administrative Expenses Implementation Directive No. 847/2021"

2. Definitions

In this Directive, unless the context requires otherwise:

1. "Administrative Expenses" means expenses which are not related to the project activities of an organization but are necessary to ensure the continued existence of an organization and related to administrative activities, and shall include: salaries and benefits of administrative employees; expenses for purchase of consumables and fixed assets; repair and maintenance expenses; office rent; parking fees; audit fees; advertisement expenses; bank service fees; utility fees; fees for fax, and internet services; postal and printing expenses; tax; expenses for purchase and repair of vehicles for administrative purposes; and procurement of oil and lubricants for the same; insurance costs, penalties and attorney fees;

የነዳጅና ዘይት እንዲሁም የመድኀን ግዢ ወጪዎችን፣ የቅጣት ክፍያዎችን፣ እንዲሁም የጥብቅና አገልግሎት ክፍያን ያካትታል።

2/ "አዋጅ" ማለት የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 1113/2011 ነው፤

2. "Proclamation" means the Organizations of Civil Societies Proclamation No.1113/2019;

3/ "ባለስልጣን" ማለት በአዋጁ አንቀጽ 4 እና የፌዴራል መንግስት የአስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 መሰረት የተቋቋመው የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን ነው፤

3. "Authority" mean the Authority for Civil Society Organizations established under Article 4 of the Proclamation & in accordance to definition and duties of the executive organs of the federal government proclamation No. 1263/2021

4/ "ድርጅት" ማለት ለጠቅላላው ሕዝብ ወይም ለሦስተኛ ወገን ጥቅም መሥራትን ዓላማ አድርጎ የተቋቋመ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅት ነው፤

4. "Organization" shall mean: a civil society organization established for the benefit of the general public or that of third parties;

5/ "ፕሮጀክት" ማለት የተወሰኑ ዓላማዎችን ከግብ ለማድረስ በታወቀ የጊዜ ሰሌዳ፣ ወጪና የአፈጻጸም መለኪያዎች የሚከናወኑ የታወቀ መነሻና መድረሻ ያለው ሥራ ሲሆን የድርጅቱን ዓላማ ለማሳካት የሚያግዙ ሌሎች ተዛማጅ ሥራዎችን ይጨምራል፤

5. "Project" shall mean: an activity undertaken within a specified timeframe, cost and implementation parameters having a specific beginning and end, and shall include the day-to-day activities an organization carries out in order to meet its objectives.

6/ በአዋጁ የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህ

6. Definitions of the Proclamation shall also

መመሪያም ተፈፃሚ ይሆናሉ፡

7/ በዚህ መመሪያ ውስጥ ለወንድ ፆታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል፡፡

be applicable to this Directive.

7. Reference to the masculine gender shall also include the feminine.

3. የተፈፃሚነት ወሰን

1. ይህ መመሪያ ተፈፃሚ የሚሆነው ለጠቅላላው ህዝብ ወይም ለሶስተኛ ወገን ጥቅም መስራትን ዓላማ አድርገው በተቋቋሙ ድርጅቶች ላይ ነው፡፡

2. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 እንደተጠበቀ ሆኖ የአባላት ጥቅምን እንዲሁም የጠቅላላው ህዝብ ወይም የሶስተኛ ወገን ጥቅምን ቀላቅለው የሚሰሩ ድርጅቶች ከሆኑ ለጠቅላላው ህዝብ ወይም ለሶስተኛ ወገን ጥቅም በሚሰሩት ስራ ላይ ብቻ ይህ መመሪያ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

3. Scope of Application

1. This Directive shall be applicable to Organizations that were established for the benefit of the general public or that of third parties.

2. Without prejudice to sub-article (1) of this Article, where organizations are established for the both the benefit of their members and that of the general public or that of third parties, this Directive shall be applicable only to their works in relation to either the benefit of the general public or that of third parties.

ክፍል ሁለት
ስለአስተዳደር ወጪ አፈጻጸም

Part Two
Implementation of Administrative Expenses

4. የወጪ ቁጥጥር ዓላማዎች

የአስተዳደር ወጪ ቁጥጥር ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡

1/ ድርጅቶቹ ከገቢያቸው ወይም ካሰባሰቡት የፋይናንስና የቁሳቁስ ሀብት ቢያንስ 80 (ሰማንያ) በመቶውን የተቋቋሙበትን ዓላማዎችና ግቦች ለማሳካት

4. Objectives of Controlling Administrative Expenses

The objectives of controlling administrative expenses are the following:

1. to ensure that organizations utilize eighty (80) percent of the financial and material resources they have raised or generated for the fulfillment of the objectives for which they are established and limit

እንዲጠቀሙበት ወይም እንዲያውሉት በማድረግ የአስተዳደር ወጪያቸውን ቢበዛ ከ20 (ሃያ) በመቶ እንዳይበልጥ ማድረግ፤

administrative expenses to not more than twenty (20) percent;

2/ የሕብረተሰቡን የላቀ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፤

2. to ensure maximum public benefit;

3/ ተቀባይነት ያለው የሂሣብ አያያዝን የተከተሉ የሂሣብ መዝገቦችን እንዲይዙ በማደረግ ተጠያቂነትና ግልጽነት እንዲኖር ማድረግ፤ እና

3. to see to it that organizations keep their books in line with accepted standards of accounting in order to ensure accountability and transparency

4/ ድርጅቶች የራስ በራስ ቁጥጥርና አስተዳደር ስርዓት በመገንባት ወጪያቸውን የሚቆጣጠሩበትን ሁኔታ ማመቻቸት።

4. to facilitate the control of expenses by organizations by putting in place self-monitoring and self-administration systems

5. ለአስተዳደር ወጪነት መሟላት ስለሚገባቸው ጉዳዮች

5. Criteria for Expenses to be Deemed Administrative

1/ አንድ ወጪ በድርጅት አስተዳደር ወጪነት ሊያዝ የሚችለው፤

1. An expense is deemed an administrative expense of an organization if:

(ሀ) ከፕሮጀክት ወጪ ጋር ያልተያያዘ ከሆነ፤

a. it is not related to the expenses of a project;

(ለ) ለድርጅቱ ህልውና ቀጣይነት አስፈላጊ ከሆነ፤

b. it is necessary for the continuity of the organization;

(ሐ) ከአስተዳደር ሥራዎች ጋር የተያያዘ ከሆነ፤

c. it related to administrative activities;

(መ) ለአስተዳደር ወጪ በተሰጠው ትርጉም ውስጥ የሚካተት ከሆነ፤ እና

d. it falls under the definition of "administrative expenses"; and

(ሠ) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 2 ንዑስ

አንቀፅ ትርጉም ውስጥ ከተካተቱት ውጭ ያለ እና በባለስልጣኑ ተቀባይነት ያገኘ ወጪ ከሆነ ነው፡፡

e. it is an expense falling outside the definition in Article 2 of this Directive but is accepted as an administrative expense by the Authority .

2/ ወጪው የአስተዳደር ወጪ መሆኑን የማስረዳት ኃላፊነት የድርጅቱ በመሆኑ በአፈጻጸም የሃያ በመቶው የአስተዳደር ወጪ ገደብ የጠበቀ መሆኑን እና በሂሣብ መግለጫ ሪፖርቱም በአግባቡ መመልከቱን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

2. As the burden of proof of showing that an expense is administrative rests on the organization, it shall make sure that the expense is within the twenty-percent limit and that the same is indicated in its financial statement report.

6. ከፕሮጀክት ጋር ያልተያያዙ ወጪዎች

6. Expenses not Related to Projects

1/ የሚከተሉት ከፕሮጀክት ጋር ያልተያያዙና በአስተዳደር ወጪዎች ውስጥ የሚካተቱ ናቸው፤

1. The following are not related to projects and are deemed to be administrative expenses:

(ሀ) ለዋናው መሥሪያ ቤት ወይም ለቅርንጫፍ መ/ቤቶች ብቻ ለዋለ ዕቃ ወይም አገልግሎት ወይም ጥቅም የወጣ ወጪ፤

a. Expense incurred for a good or service only used by the head office of an organization;

(ለ) ለዋናው መሥሪያ ቤት ወይም ለቅርንጫፍ መ/ቤቶች አገልግሎት የሚውል ተሸከርካሪ ግዢና ተያያዥ ወጪዎች፤

b. Expenses for the procurement of vehicles for head-office use and related expenses;

(ሐ) የዋናውን መሥሪያ ቤትን ወይም የቅርንጫፍ መ/ቤቶችን ሥራ ለማከናወን ለሚቀጠሩ ሠራተኞች የሚከፈል ደሞዝና ጥቅማ ጥቅሞች፤

c. Salaries and benefits for employees hired to carry out works of the head and branch offices ; and

(መ) ለዋና መሥሪያ ቤት ወይም ለቅርንጫፍ መ/ቤቶች የሚውል ማናቸውም ግንባታ፡፡

d. Any construction for the head and branch offices.

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)

2. Notwithstanding the provision of sub-article (1)

ድንጋጌ ቢኖርም፣ ዋናው መሥሪያ ቤት ፕሮጀክቱ በሚከናወንበት ቦታ /አንድ ወጥነት ባለው አደረጃጀት/ ሥራውን የሚያከናውን የሆነ እንደሆነ ከፕሮጀክት ጋር የተያያዘ ወጪ ተደርጎ ይወሰዳል።

of this article, if the head office conducts its business at a project site in an integrated manner, the expense shall be deemed a project-related expense.

7. ገቢን በግልጽ ስለማመልከት

የአንድ ድርጅት ዓመታዊ የሥራ እንቅስቃሴ ሪፖርት፣

1/ **የለጋሹን ሙሉ ስምና አድራሻ፣**

2/ **በጥሬ ገንዘብና በዓይነት የተለገሰውን መጠንና ገቢ የሆነበትን ቀን፣ ለጋሾች ጥቅም ያገኙ ወይም የሚያገኙ የሆነ እንደሆነ ያገኙትን ጥቅም፣**

3/ **አገልግሎት በመስጠት የተደረገ ልገሳ ከሆነ የአገልግሎቱን ዓይነትና ዋጋ፣ አገልግሎቱ በማን እንደተሰጠና አገልግሎቱን የሰጡ ሰዎች ቁጥር፣**

4/ **ልገሳው ለድርጅቱ ስለመግባቱ ያረጋገጠው የድርጅቱ ኃላፊ፣**

5/ **በዓይነት የተለገሰ ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ከተመለከቱት በተጨማሪ፣**

(ሀ) **የንብረቱን ዓይነት ከነሙሉ መግለጫው፣**

(ለ) **ንብረቱ ተገምቶ ከሆነ የንብረቱን ግምትና የገማቹን ሰምና አድራሻ፣ ካልተገመተ የገበያውን**

7. Clear Disclosure of Income

An organization's annual activity report shall include the following:

1. The Donors' full names and addresses;

2. Donations made in cash and in kind, the date received, and the benefits (if any) donors received or will receive;

3. Where donation is in the form of service, the type and [monetary] value of the service provided and the number of persons who provided the service;

4. The [name] of the organization's official that confirmed that the donation was received.

5. Where donation is made in kind, the following shall be included in addition to those specified in sub-article (2):

   a. The type of asset with its full description; and

   b. If the asset was valued, its value and the name and address of the valuer; if not valued, the market value of the same.

ዋጋ፤

የሚያካትት መሆን ይኖርበታል፡፡

6/ አገልግሎት በመስጠት የተለገሰ ከሆነ በባለሙያ የተገመተው የአገልግሎት ዋጋ ወይም የገበያ ዋጋ መገለጽ ይኖርበታል፡፡

6. For a donation of service, the value of the service assessed by a professional or the market value of the same shall be indicated.

7/ ለጋሾች ከልገሳ ጋር በተያያዘ ያስቀመጡት ገደብ ካለ ይኸው መገለጽ ይኖርበታል፡፡

7. Any restrictions specified by donors in respect of a donation shall be disclosed.

8. የአስተዳደራዊ ወጪ ተፈጻሚ ስለማይሆንባቸው ድርጅቶች

8. Organizations Exempted from Administrative Expenses

1) የሚከተሉት ድርጅቶች ወይም ለሚከተሉት ስራዎች የሚወጡ ወጪዎች የሃያ በመቶ የአስተዳደራዊ ወጪ ገደብ ተፈጻሚ አይሆንባቸውም፤

1. The following organizations or expenses of the following works are exempted from the twenty-percent cap on administrative expenses:

(ሀ) መንግሥት ቅድሚያ ለሰጣቸውና ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ለሚሰጥ አገልግሎት፤

a. Service rendered to parts of the society that are prioritized by the government as needing special support;

(ለ) ለአስቸኳይና ድንገተኛ እርዳታ ስራዎች

b. Organizations rendering emergency relief and assistance services ;

(ሐ) ቃል የተገባላቸው ገንዘብ በመቅረቱ ምክንያት ከፍተኛ የበጀት እጥረት የገጠመው ድርጅት፤

c. Organizations facing severe budget deficits due to donors' failure to fulfil their promises;

(መ) ለመንግሥት ወይም ለሕዝብ ጥቅም የጥናትና ምርምር ሥራዎች የሚያከናውን ድርጅት፤

d. Organizations that conduct studies and research activities for public or government benefit;

(ሠ) በጀቱ ከብር 2,000,000 (ከሁለት ሚሊዮን ብር) ያልበለጠ ድርጅት፤

e. Organizations whose budget is not more than two million Birr (Birr 2,000,000);

(ረ) አዲስ በባለስልጣኑ የተመዘገቡ አገር በቀል ድርጅቶች ስራ ለመጀመር በሚያስችል ደረጃ እንዲቋቋሙ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ የሚያወጡት የመቋቋሚያ ወጪ፤

f. Formation expenses which will enable newly-established indigenous organizations that are registered at the to Authority commence operations within a period of one year; and

(ሰ) ድርጅቱ የተቋቋመበትን ዓላማ ለማስፈጸም አስፈላጊ የሆነ የሥራ ዘርፍን ለማጠናከር የሚሰጥ የትምህርት ዕድል ወይም የስልጠና ወጪ፤

g. Education opportunities that strengthen the work area that is paramount in accomplishing the objectives of the organization.

2) ባለስልጣኑ የአንድ ድርጅትን የፋይናንስ አቋም እንዲሁም ድርጅቱ የተቋቋመበትን ዓላማና ለሕዝብ የሚኖረውን ጠቀሜታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ድርጅቱ ለተወሰነ ጊዜ የሃያ በመቶ ገደብ ተፈጻሚ እንዳይሆንበት ማድረግ ይችላል፡፡

2. The Authority may, by taking into consideration the objectives of an organization and the benefit of the public, exempt the same from the twenty-percent cap for a limited period of time.

3) በዚህ አንቀፅ መሰረት የሃያ በመቶ አስተዳደራዊ ወጪ ገደብ ተፈፃሚ የማይሆነው ድርጅቱ በአዋጁ የተቀመጠውን የሃያ በመቶ ገደብ ጠብቆ መስራት ያልቻለ መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡

3. Organizations may only be exempted from the twenty-percent cap where it is proven that they are unable to observe the same.

4) የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀፅ 1 ቢኖርም በማናቸውም ሁኔታ ቀሪ የሚሆነው የሃያ በመቶ አስተዳደራዊ ወጪ ገደብ ከ 50 ፐርሰንት መብለጥ የለበትም፡፡ ሆኖም የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር አሳማኝ ምክንያት መኖሩን ያረጋገጠ እንደሆነ በልዩ ሁኔታ የገደቡን መጠን

4. Notwithstanding sub-article (1) of this Article, the exemption from the twenty-percent administrative expense cap may, in no case, exceed fifty percent. However, the Director-General of the Authority may raise or lift the restriction altogether upon ascertaining that there is good cause to do so.

ከፍ ሊያደርገው ወይም ሙሉ በሙሉ ሊያነሳው ይችላል፡፡

9. ሰለሂሣብ መግለጫ

1/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ማናቸውም ድርጅት በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የድርጅቱን የሀብትና ዕዳ፣ የሀብት ለውጥ እና የጥሬ ገንዘብ ፍሰት መግለጫዎች እንዲሁም በእነዚህ የቀረቡ የማብራሪያ ማስታወሻዎችን ያካተተና በውጭ ኦዲተሮች የተመረመረ የሂሣብ መግለጫ ለባለስልጣኑ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚዘጋጅ የሂሣብ መግለጫ የአስተዳዳር ወጪን ሃያ በመቶ ገደብ በግልጽ ማሳየት አለበት፡፡

3/ ጠቅላላ የሀብት መጠን ከብር 200,000 (ሁለት መቶ ሺህ) ያልበለጠ ድርጅት የሂሣብ መግለጫውን በውጪ ኦዲተሮች እንዲያስመረምር አይገደድም፡፡

9. Financial Statements

1. Without prejudice to the provisions of Sub-article (2) of this article, any organization shall, the end of a budget year, submit a financial statement to the Authority which is examined by external auditors and shows assets and liabilities; change in assets and cash-flow statements of the organization together with explanatory notes.

2. A financial statement prepared in accordance with sub-article (1) of this article shall comply with the twenty-percent cap.

3. An organization whose total asset is not more than two-hundred thousand Birr (Birr 200,000) shall not be obliged to have its financial statements examined by external auditors.

10. የሃያ በመቶ ገደብ ስላላከበረ ድርጅት

1/ የሃያ በመቶ ገደብን ያላከበረ ድርጅት፣

(ሀ) መታረም የሚችል የሆነ እንደሆነ እንደገና በ30 ቀናት ውስጥ

10. Organizations Failing to Comply with the Twenty-Percent Cap

1. An organization that fails to comply with the twenty-percent cap:

   a. Will be given an opportunity to comply with the requirement

እንዲያስተካክል ይፈቀድለታል፤

within 30 days.

(ለ) ሊታረም የማይችልና ጥፋቱ የመጀመሪያ የሆነ እንደሆነ የመጀመሪ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፤

b. Where compliance could not be obtained and the failure to comply happened for the first time, the organization shall be given a first written warning.

(ሐ) ለሁለተኛ ጊዜ የደገመ እንደሆነ የመጨረሻ ጥብቅ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፤

c. Where non-compliance happened for a second time, the organization shall be given a strict final warning.

(መ) ከሁለት ጊዜ በላይ ጥሰት የፈጸመ እንደሆነ ባለስልጣኑ የድርጅቱ የሥራ አመራሮች ላይ ተመጣጣኝ እርምጃ እንዲወሰድ ለድርጅቱ የበላይ አካል ያሳውቃል፡፡

d. Where non-compliance happened for more than twice, the Authority shall inform the governance body of the organization to take proportional action against the management.

2) በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 1 (መ) መሰረት እርምጃ እንዲወሰድ የተመራለት ድርጅት በ30 ቀናት ውስጥ ምንም አይነት እርምጃ ካልወሰደ ወይም የወሰደው እርምጃ ተመጣጣኝ ካልሆነ የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር አግባብ ባለው የአዋጁ ድንጋጌና መመሪያ መሰረት ድርጅቱ ታግዶ ምርምራ እንዲደረግ ይወስናል፡፡

2. Where the organization that was directed to take action under sub-article (1) (d) fails to do within thirty days or where the actions takes are not commensurate, the Authority shall, according to the relevant provision of the Proclamation, decide to suspend the organization and have an investigation conducted.

3) በየትኛውም የበጀት ዓመት በቀረበ የኦዲት ሪፖርት የአስተዳደራዊ ወጪው ከ40 በመቶ በልጦ የተገኘ እንደሆነ ባለስልጣኑ በአዋጁ መሰረት ድርጅቱ እንዲፈርስ ለቦርዱ ለውሳኔ

3. Where administrative expenses in an audit report submitted for any budget year exceed 40 percent, the Authority shall recommend to the Board that the organization be dissolved

ያቀርባል፣

according to the Proclamation.

ክፍል አራት

ልዩ ልዩ ድንጌዎች

Part Four

Miscellaneous Provisions

11. የፕሮጀክት ወጪን ስለመቆጣጠር

ማናቸውም ድርጅት ለፕሮጀክት የሚወጡ ወጪዎች ድርጅቱ የተቋቋመበትን ዓላማ ለማጎልበትና ለማጠናከር የዋለ መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡

11. Controlling Project Expenses

Any organization has the responsibility to ensure that project expenses are utilized to strengthen and enrich the objectives of the organization.

12. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ መመሪያ ከፀናበት ቀን ጀምሮ የሚቀርቡ ያለፈው የበጀት ዓመት የሥራ እንቅስቃሴ ሪፖርትና የሂሣብ መግለጫ በ70/30 ላይ የተመሠረተ ቢሆንም በአዋጁ የተደነገጉትን መብቶች መጠቀምን አይከለክልም፡፡

12. Transitory Provision

Organizations submitting activity reports and financial statements of the previous budget year on the basis of the 70/30 arrangement and after the coming into force of this directive are not precluded from making use of the rights provided in the Proclamation

13. መመሪያው ስለሚሻሻልበት ሁኔታ

ባለስልጣኑ ይህንን መመሪያ በማናቸውም ጊዜ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

13. Amendment

The Authority may amend this directive at any time.

14. ስለተሻረና ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው መመሪያዎች

1/ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት የዓላማ ማስፈፀሚያና የአስተዳደራዊ ወጪዎችን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 2/2003 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

2/ ማናቸውም ሌላ መመሪያ ወይም

14. Repealed and Inapplicable Directives

1. The Directive to Determine the Operational and Administrative Costs of Charities and Societies N0. 2/2011 is hereby repealed.

ልማዳዊ አሠራር በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

2. Any other directive or customary practice shall not be applicable to matters covered by this Directive.

15. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ከተፈረመ በኋላ በኢፌዲሪ የፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በባለስልጣኑ ድህረገጽ ይፋ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

15. Effective Date

This Directive shall enter into force on the day it is publicized by the authority's website after registered by the Ministry of Justice and signed by the Director General of the Authority.

ጂማ ዲልቦ ደንበል
የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን
ዋና ዳይሬክተር
ጥቅምት 26 ቀን 2014 ዓ.ም

Jima Dilbo Denbel
Director-General
Authority for Civil Society Organizations
November 06,2021